DMU

Advanced Journal of Interdisciplinary Studies 8(2024) 1328-1349

AJIDS

Journal homepage: www.ajids.com.et

**Volume 8(2), Dec 2024**

# የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች፤ ጥበባዊ ፋይዳዎች፤ አሁናዊ ተግዳሮቶች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች በጎዛምን ወረዳ ማኅበረሰብ ተተኳሪነት

Mesfin Fekadie*

Department of Ethiopian Language and literature Amharic, College of Social Science and Humanities, Debre Markos University, Debre Markos, Ethiopia

*Corresponding Author's Email: *mesfin_fekadie@dmu.edu.et*

## አኅጽሮተ ጥናት

*ይህ ጥናት "የአብነት ትምህርት የአስተምሮ ደረጃዎች፤ ጥበባዊ ፋይዳዎች ፤ አሁናዊ ተግዳሮቶች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች በጎዛምን ወረዳ ማኅበረሰብ ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ የተሰራ ነው። የጥናቱ ዐቢይ ዓላማም የአብነት ትምህርት የአስተምሮ ደረጃዎችን፤ጥበባዊ ፋይዳዎችን እና ተማሪዎች ያሉባቸዉን አሁናዊ ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ መፈተሽ እና የመፍትሔ ሀሳብ መስጠት ነው። ለጥናቱ ዓላማዎች ምላሽ ለመስጠት የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች ምን ምን ናቸዉ? በእያንዳንዱ የትምህርት እርከን ስር ምን ምን ዓይነት ትምህርቶች ይሰጣሉ? ተማሪዎች ከማስተማሩ ጎን ለጎን ምን አይነት ጥበቦችን ይገበያሉ? የአብነት ተማሪዎቸ አሁናዊ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸዉ? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች መነሻ አድርጓል። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችም በሙያው ላይ የጠለቀ ዕውቀት ካካበቱ ከድጓ፣ ከዜማ፣ ከቅኔ መምህራን፣ ከአብነት ተማሪዎች እና ከታላላቅ መንፈሳዊ አባቶች የምልከታ፣ የቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎች በጽሑፍ፣ በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ፣ በቪዲዮ ካሜራዎች እንዲያዙ ተደርጓል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም በዓይነት በዓይነት ተደራጅተው በገላጭ ስልት ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም ተተንትነው ቀርበዋል። በትንታኔው መሠረት በጥናቱ ተተኳሪ ማኀበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የአብነት ትምህርት ቤቶች የንባብ፣ የቋንቋ፣ የዜማ፣ የቅኔ እና የቁጥር ቤት የሚባሉ የትምህርት እርከኖች እንዳሏቸዉ ታይቷል። በተለይ የቅኔ ቤት ፈጠራ (Creativity) የሚታይበትና ጥልቅ የመረዳት ችሎታ (Deep understanding) የሚስተዋልበት መሆኑን ለመረጋገጥ ተችሏል። ከትምህርታቸዉ ጎን ለጎን የአብነት ተማሪዎች የተለያዩ ክህሎቶችን (Skills) ለምሳሌ፡- የቁም ጽህፈት፣ የባህል ህክምና ፣የብራና አወጣጥ፣ የመጻሕፍት ድጎሳና ቁነና እየተማሩ በኢኮኖሚ ራሳቸዉን እንደሚደግፉ ለማየት ተችሏል። ይሁን እንጅ በአሁኑ ሰዓት የአብነት ተማሪዎች ፈርጀ ብዙ የሆኑ ችግሮች እያጋጠሟቸዉ መሆኑ ታይቷል፤ ከችግሮቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- የመጠለያ፣ የምግብ አቅርቦት፣የመጸዳጃ ችግሮች ተጠቃሾች ናቸዉ። በመሆኑም በአብንነት ትምህርት ቤቶች እየተሰጡ ያሉ ዕውቀቶች ፣ ከዕዉቀቱ ጎን ለጎን የሚያዳብሩት ጥበባትና ሰብዕናቸዉን የሚገነቡባቸዉ እሴቶች ከነአካቴው ከመጥፋታቸው በፊት ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት ማኅበረሰቡ፣የባህል ቱሪዝም ባለሙያዎች እና መሰል ባድርሻ አካላት አፋጣኝ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን እንዲፈልጉ ምክረ ሀሳብ በመጠቆም ጥናቱ ተቋጭቷል።*

**ቁልፍ ቃላት፡-** *የአብነት ትምህርት፣የአስተምህሮ ደረጃዎች፣ አሁናዊ ተግዳሮቶ.*

# Traditional Education Levels; Artistic Benefits, Current Challenges and Solutions in Gozamen District Community in Focuse


## Abstract

*This research is about"Traditional Education Levels; Artistic Benefits and Current Challenges in East Gojam Zone, Gozamen District Community in Focuse" What are the educational levels of traditional education in the educational process? Besides in teaching, what kind of skills do students trade? What are the current challenges that traditional education students are facing? These basic questions are the focus of the research. The information needed for the study was collected from the leading "kedigwa, kezēma, kek'inē merī gētochi and great spiritual fathers and students" who have gained in-depth knowledge in the profession through observation, interview and group discussion methods. The collected data were organized by type and analyzed using descriptive method and functional theory. According to the analysis, it was seen that the traditional schools in the community of the study have 'yefdeli, yenibabi, yek'wanik'wa, yezma, yek'in, and yek'ut'iri bti'. It was confirmed that the 'yek'in is the place where creativity and profound understanding can be observed. It has been observed that there are currently many problems facing students in traditional schools. Shelter, food supply, and toilet facilities are among the main ones mentioned. Since the students are forced to build their own shelters and eat their food "for the glory of Mary, for the glory of the Light", the teaching is "Independent learning"; In their struggle to overcome these problems, data indicates that they are getting distracted from their education while entering the city and doing various labor jobs.. Therefore, before the knowledge that is being imparted in the traditional schools, the sector deserves attention from society because the skills that develop along with knowledge and the values that form human beings are being lost. It is important for cultural tourism bodies and similar stakeholders to search for immediate solutions.*


**Key words:** *Abenet Education, Education Levelss, Current Challenges*

## 1. መግቢያ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ የትኩረት አቅጣጫ የአብነት ትምህርት አሰጣጥ የአስተምህሮ ደረጃዎች፣ ዓይነቶች፣ ፋይዳቸውና በዘርፉ ላይ እየተከሰቱ የሚገኙ አሁናዊ ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ ማሳየት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማሳየት ላይ ነዉ።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የአብነት ትምህርት ቤት ከአባት የተገኘ ከአበው የተወረሰ ከጥንት የነበረ፣ የማንነት መገለጫ፣ በራስ ቋንቋ በራስ ፊደል፣ በራስ ስርዓተ ትምህርት፣ የሚሰጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ትምህርት መሆኑ ይገለጻል ልዑለቃል አካሉ(2000)[1] ፤(ሀብተ ማርያም፣1963)። ስርዐተ ትምህርቱ አገር በቀል በሆኑ ሊቃውንት የሚዘጋጅ ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜም እየበለጸገና እየዳበረ የሚሄድ ነው። የአብነት ትምህርት ቤት በልማድ «የቆሎ ትምህርት ቤት» በመባል ይጠራል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ «የቄስ ትምህርት ቤት» እንዲሁም ሌሎቹ «የቤተ ክህነት ትምህርት ቤት» በተመሳሳይ «መንፈሳዊ ትምህርት ቤት» በማለት ይጠሩታል (ዘላለም፡2011)፤(ኪዳነ ማርያም፣1954)። እንደ (አባ ጎርጎሪዎስ፡ 1974) አገላለጽ አብነት ማለት

እግዚአብሔር ዓለምንና ሰውን ሲፈጥር ከእግዚአብሔር የታሰበ ለአባቶች የተሰጠ ማለት ነው። እንደ ሊቃዉንት አገላለጽ እግዚአብሔር የመጀመሪያው አስተማሪ ሁኖ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት በዘመነ አበው ለአባቶች ስላስተማረ የሱን አስተምህሮ እና ምሳሌ መከተል አብነት ይባላል።

የአብነት ትምህርት ቤቶች ከባድ የማኅበራዊ ኑሮና የመንፈሳዊ ሕይወት ማሳኪያ መሣሪያዎች በመሆን ካገለገሉ ሌሎች በርካታ ባህላዊ ተቋማትና እሴቶች መካከል ቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው (Pankhurst :1974)። አብነት ትምህርት ቤቶች በዋናነት የሚታወቁት ለቤተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ የተካኑ የሃይማኖት ባለሙያዎችን ለማሰልጠን በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ነው (Pankhurst፡1969)። ነገር ግን ሁለገብ የሆኑት የአብነት ትምህርት ቤቶች ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጎን ለጎን ለዓለማዊ ህይወት የሚያገለግሉ የተለያዩ ክህሎቶች የሚገበይበት የዕውቀት ማዕድ መሆናቸው በጥናት ላይ ተመስርቶ አልተዳሰሰም፤ለምሳሌ፡- በአብነት ትምህርት ቤቶች የአስተምህሮት ስርዓት ከሚገበዩ ዕውቀቶች መካከል የብራና አፋፋቅ፣ የቀለም እና የብዕር አዘገጃጀት ፣ የፊደል አጣጣል፣ የነጥብ አቀማመጥ ፣ የቀለም ቅብ ፣ የሐረግ እና የሥዕል ንድፍ ፣ መጻሕፍት ጥረዛ፣ መጻሕፍት ኩተታ እና ድጎሳ ዋና ዋናዎቹ ናቸው( መንግስቱ ጎበዜ፣2002)፤(መርሻ አለኸኝ፣2011) ፤(ሀብተ ማርያም፣1963)።

ከአብነት ትምህርት ጋር በተያየዘ ከተሰሩ ጥናቶች መካከል የ(ጓላሸት፣ 2009)፣ የ(ጸጋዬ፣ 2008)፣ የ(ፍሬህይወት፣ 2008)፣ የ(ጎይለየሱስ፣ 2008) ፣የ(መንግስቱ ጎበዜ፣2002) እና የ(እነከበደ፣ 2006) ተዳሰዋል። የቀረቡት ጥናቶች ከዚህ ስራ ጋር የሚያመሳስላቸው የጥናቶቹ የትኩረት አቅጣጫ የአብነት ትምህርት መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ጥናት በተተኳሪው ማኅበረሰብ ውስጥ የሚካሄደዉን የአብነት ትምህርት እና የአስተምህሮ ደረጃዎች ጥበባዊ ፋይዳዎች፤አሁናዊ ተግዳሮቶች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች በዝርዝር በመዳሰስ ትምህርቱ የአካባቢውን ማኅበረሰብ እምነት፣ባህል እና ልማድ ግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ከመንፈሳዊ ዕውቀት ባሻገር የተማሯቸዉን ዕዉቀቶችና ክህሎቶችን በዓለማዊ ህይወታቸዉ በምን መልኩ እንደሚገለገሉባቸዉ የሚመረምርና የመፍትሔ ሀሳቦችን ከጥናቱ በመነጨ መረጃ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ስለሆነ ከፍ ሲል ከቀረቡት ጥናቶች በእጅጉ ይለያል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የአብነት ትምህርት ረጅም ዘመን ያስቆጠረና በትዉልድ ቅብብሎሽ ዛሬ ላይ የደረሰ መሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ (ኃይለገብርኤል፣2007)። ዘመናዊ ትምህርት እንደዛሬዉ በአገራችን ሳይስፋፋ አብዛኛዉ የኅብረተሰብ ክፍል ማንበብና መጻፍ የቻለዉና ከማሐይምነት የተላቀቀዉ በዚሁ የአስተምህሮ ስርዓት አማካኝነት ነዉ (ኪዳነ ማርያም፣1954)። የአገሪቱ በርካታ ዕዉቀቶች፣ ክህሎቶች እና እሴቶች የተቀዱት ከዚሁ የአስተምህሮ ስርዓት ነዉ (መርሻ አለኸኝ፣2011)። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት የአስተምህሮ ስርዓቱ እየተዳከመ በመምጣት ላይ መሆኑንን መረጃዎች

ያሳያሉ፡፡ በተለይ ጥልቅ ፍልስፍና የሚታይባቸዉ የቅኔ እና የቁጥር ቤቶች እጅግ እየተዳከሙ በመምጣት ላይ ይገኛሉ(ሀብተ ማርያም፣1963)፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት መጠናት አነሳሽ ምክንያቶቹ፡-

1. የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ስርዓት እና የትምህርቱ እርከኖች ምን ምን እንደሆኑ ለማወቅ ያለ ፍላጎት፤
2. በእያንዳንዱ የአብነት የትምህርት እርከን ስር የሚሰጡ የትምህርት ይዘቶች ምን አይነት ርዕሰ ጉዳዮችን እንደሚይዙ ለመፈተሸ፤
3. ከመሰረታዊ የአብነት ትምህርቱ ጎን ለጎን ተማሪዎች ዓለማዊ ህይወታቸዉን ለመግፋት የሚቀስሟቸዉ ክህሎቶች ምን ምን እንደሆኑ ለማብራራት፤
4. በአብነት ትምህርቱ ላይ ትምህርቱን የሚከታተሉ ተማሪዎች እና የአካባቢዉ ማኅበረሰብ ያላቸዉ አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማወቅ፤
5. በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ አካባቢ የአብነት ተማሪዎቹ እያጋጠሟቸዉ ያሉ አሁናዊ ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ በመለየት በጥናት የተደገፈ የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ ያለ ፍላጎት ዋና የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

“የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች፤ ጥበባዊ ፋይዳዎች ፤አሁናዊ ተግዳሮቶች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች በጎዛምን ወረዳ ማኅበረሰብ ተተኳሪነት” ላይ ትኩረት ያደረገው ይህ ጥናት በሂደቱና በአተገባበሩ ለሚከተሉት ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

- ✓ የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ሥርዓት፤ የትምህርት እርከኖች ምን ምን ናቸዉ?
- ✓ በእያንዳንዱ የትምህርት እርከን ስር የሚሠጡ የትምህረት ይዘቶች ምን ምን ናቸዉ?
- ✓ ከመሰረታዊ ትምህርቱ ጎን ለጎን ተማሪዎች የሚቀስሟቸዉ ጥበቦች ምንድናቸዉ?
- ✓ በአብነት ትምህርቱ ላይ ትምህርቱን የሚከታተሉ ተማሪዎች እና የአካባቢዉ ማኅበረሰብ ያላቸዉ አመለካከት ምንድን ነዉ?
- ✓ ተማሪዎቹ እያጋጠሟቸዉ ያሉ አሁናዊ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸዉ? የሚሉት ይገኙበታል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1. ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ “የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች፤ ጥበባዊ ፋይዳዎች እና አሁናዊ ተግዳሮቶች ” ምን እንደሚመስሉ መፈተሸ ነዉ፡፡

### 1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ ዋና ዓላማዉን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ለማሳካት ተካሂዷል፡፡

- ✓ የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ሥርዓት፤ የትምህርት እርከኖች ምን ምን እንደሆኑ መግለጽ፤

- ✓ በእያንዳንዱ የትምህርት እርከን ስር የሚሰጡ የትምህርት ይዘቶች ምን ምን እንደሆኑ ማብራራት፤
- ✓ ከመሰረታዊ ትምህርቱ ጎን ለጎን ተማሪዎች የሚቀስሟቸዉን ጥበቦች መዘርዘር፤
- ✓ ተማሪዎቹ እያጋጠሟቸዉ ያሉ አሁናዊ ተግዳሮቶችን መለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማሳየት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

### 1.5. ንድፈ-ሀሳባዊ ማእቀፍ (Theoretical Framework)


ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውንም ነገር ያለውን ተግባር እና አገልግሎት ለመመርመር እንደሚረዳ Okpewho (1992:75) ያስረዳል፡፡ በዚህ ጥናት ዉስጥ የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ስርዓት፤ጥበባዊ ፋይዳዎች እና ተማሪዎች ያሉባቸዉን አሁናዊ ተግዳሮቶች ለመግለጽና በመረጃዎች አስደግፎ ለመተንተን ንድፈ ሀሳቡ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 1.6. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

ጎዛምን [1] በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ የስያሜ አመጣጥ ጎዜ በመባል ይታወቅ የነበረ ሰው ከወሎ ተሻግሮ ጎጃም መንግስት ከተባለ ቦታ ላይ ቤተ መንግስት መሰረተ፡፡ ከዚያም ወደ አራት መከራክር በመሄድ አራት መከራክር ላይ ትንንሽ ጎጆዎች ሰርተው ይኖሩ እንደነበርና በተሰሩ ጎጆዎች አማካኝነት ጎዣሜ የሚል ስም ተሰጣቸው፡፡ ጎዜ አራት መከራክር ላይ ደረቤና ሰረቤን ይወልዳል፡፡ ቦታውን አካፈላቸው፡፡ የሰረቤና የደረቤ የይዞታ ድንበር የዛሬው ጌደብ ነው፡፡ ግራው ለሰረቤ፤ ቀኙ ለደረቤ ሁኗል፡፡ ደረቤ ጎዛምንን፣ አዋበልን፣ አነደድን፣ ጥላት ግንን ይወልዳል፡፡ በዚያው ጎዛምን ለደረቤ የበኩር ልጁ ነው አለቃ ተክለ እሱስ ዋቅጅራ(የጎጃም ትዉልድ ከዓባይ እስከ ዓባይ፣2003)፡፡ ጎዛምን ወረዳ ውስጥ ሃያ አምስት (25) የገጠር ቀበሌዎችና አምስት ታዳጊ ከተማዎች በድምሩ ሠላሳ (30) ቀበሌዎች የሚገኙ ሲሆን ወረዳው ከክልሉ ዋና ከተማ ከባህርዳር 265 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከአገሪቱ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ደግሞ 300 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

---

*4.ሊቀ ኅሩያን በላይ መኮንን ደግሞ ጎጃምን ካስገኘው የጋፋት ቃል ጉዛም (ትርጉሙ ለምና ባለጠጋ መሬት ነው ይላሉ) ጋር ያዛምዱታል፤ (ዝርዝሩን እቴጌ ጣይቱ በደብረ መዊእ፣ 2006 ዓ.ም ይመልከቱ) ፡፡*




ለጥናት የተመረጡ ቀበሌዎች:- 1. እነራታ፣ 2. ለቅለቂታ፣ 3. ዉገር

## 2. የጥናቱ ሥነ ዘዴ

### 2.1. የጥናቱ ንድፍ (Study Design)

ጥናቱ በአብነት ትምህርት የአስተምሮ ስርዓት ምንነት፤ በትምህርቱ የእርከን ደረጃዎች፤ በክህሎታዊ ፋይዳዎች እና አሁናዊ ተግዳሮቶች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ዓይነታዊ ነው፡፡ ዓይነታዊ ምርምር አንድን ጉዳይ አንስቶ ጉዳዩ ምን እንደሚመስል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ ስለነገሩ ምንነትና ትክክለኛ ባህርይ ሰፊና የዳበረ ማብራሪያ የሚሰጥበት ነው (Best, 1981፣254)፡፡ በመሆኑም በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከመስክ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች በገለጻና ትንተና ዘዴዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 2.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለጥናቱ የተመረጠዉ የንሞና ዘዴ ዓላማ ተኮር ነዉ፡፡ ያለው (1998፡312) ስለ ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ሲገልጹ፤ "ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች እና ተተኳሪዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ነው፡፡ እነማንን ብመርጥ የሚፈለገው መረጃ ኑሯቸው ሊሰጡኝ ይቻላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የጥናቱን አካላይ እና መረጃ የሚሰጡ ሰዎችን ይመርጣል" ይላሉ፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ ጎዛምን ወረዳ ከሚገኙ ሰላሳ (30) የአብነት ትምህርት ቤቶች መካከል በስምንቱ(8) ቀበሌዎች ከሚገኙ የአብነት ትምህርት አስተማሪዎች እናተማሪዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እንዲሁም በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ አማካኝነት ከፍተኛ የተማሪ ቁጥር ያላቸዉ፣ነባር እና ሁሉንም የአብነት የትምህርት እርከኖች እየሰጡ ካሉ እንዲሁም በቂ መምህራን ያላቸዉ ዘጠኝ (9) የወረዳዉ ቀበሌዎች በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል፤ እነሱም:- ቸር ተከል፣ ፈንደቃ፣ ለቅለቂታ፣ የቦቅላ፣ ወይንማ ገራሞ፣ ጭምቦርድ፣ የጥጃን፣ ወንቃ እና እነራታ ናቸዉ፡፡

### 2.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በዋናነት ቃለ መጠየቅ ፣ ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠየቅ እና የቡድን ውይይት እንደሆኑ ያለው ይገልጻሉ(1998፡47)፡፡ ከዘዴዎች ውስጥ በጥናቱ ዉስጥ ተግባር ላይ የዋሉት ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ውይይት ናቸዉ፡፡ እነዚህን ዘዴዎች የተመረጡበት ምክንያት

በምልከታ የተማሪዎችን የአስተምህሮ ስርዓት በመመልከት መረጃ ለመሰብሰብ ሲሆን፤ በቃለ መጠይቅ ደግሞ ስለትምህርቱ ከትምህርቱ ጎን ለጎን ስለሚማሯቸዉ ክህሎቶች፣ ስለአሁናዊ ተግዳሮቶቻቸዉ በሰፊዉ መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የቡድን ውይይትን በመጠቀም የተሟሉ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 2.4. የጥናቱ መተንተኛ ዘዴ

በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የተሰበሰበን መረጃ እንዴት መተንተን እንደሚቻል Dawson (2002፡110) ሲገልፁ፡-መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ የምርምር ዕቅድ በማዘጋጀት የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ መረጃዎችን አደራጅቶ መተንተን ይገባል፡፡ በጥናቱም ሊደረጉ የሚገባቸዉ ንጽጽሮች እና ትንታኔዎች ሁሉም ተዛማጅ መረጃዎች መገኘታቸውን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው፤ ስልታዊ በሆነ መንገድ ማደራጀት ማለትም፡- ኮድ መስጠት፣ መመደብ እና ማቧደን ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከመስክ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች በገለጻና ትንተና ዘዴዎች ተተንትነዉ ቀርበዋል፡፡

## 3. መረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ከሆነው ከመስክ በምልከታ፣በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ዉይይት እንዲሁም ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ከቤተ መጻሕፍት፣ከታማኝ ድህረ ገጾች እና የመመረቂያ ዲማጾች የተገኙ መረጃዎች በዓይነት በዓይነት ተደራጅተው ተተንትነዉ ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ስርዓት ምንነት

በጥናቱ ተተኳሪ የአብነት ት/ቤቶች የሚካሄደዉ የአስተምህሮ ስርዓት የራሱ የሆኑ ባህርያቶች አሉት፡፡ ተማሪዎቹ ትምህርታቸዉን ለመከታተል መጀመሪያ በአካባቢዉ ከሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች ማለትም፡- ሳር፣ ጨፈቃ፣ ሰንበሌጥ፣ እንጨት ከመሳሰሉ ነገሮች ጎጆ መቀለስ ይጠበቅባቸዋል (ተሳታፊ 5፣እድሜ68 ዓመት፣የድጓ መሪጌታ)፤ (ኪዳነ ማርያም፣1954)፡፡ይህን ካደረጉ በኋላ ከሚያስተምሯቸዉ የኔታ በሚወጣላቸዉ የትምህርት ፕሮግራም መሰረት ትምህርታቸዉን በቀንና በማታ በትኩረት ይከታተላሉ፡፡ የሚመገቡትንም የዕለት ምግብ ከምዕመናን ቁራሽ በመለመን ያገኛሉ፡፡ በትምህርቱ ፍልስፍና መሰረት ከወላጅ አሳዳጊ ጋር ሆኖ የሞቀ የላመ ምግብ እየተመገቡ መኖር በትምህርቱ ለመግፋትም ሆነ ጠንካራ ሆኖ ችግርን ተቋቁሞ እሚፈለገዉ ደረጃ ላይ ለመድረስ አይቻልም የሚል እሳቤ ያለ በመሆኑ በዚህ ትምህርት ለመዝለቅ ከወዳጅ ዘመድ እርቆ መሄድ፤ወዳጅ ዘመድ አሉበት ድረስ በመምጣት ትምህርታቸውን እንዳያደናቅፉ ሲባል ስማቸውን ሁሉ መቀየር አንዱ የትምህርቱ መገለጫ ነዉ (ተሳታፊ 7፣ እድሜ70 ዓመት፣የድጓ መምህር)፡፡ የዓመት ልብስም ሆነ የዕለት ጉርስ የሚያሟሉት ለነፍሱ ካደረ ምእመን ስለሆነ ያገኙትን ምግብም ሆነ ልብስ በቁጠባ ይጠቀማሉ (ተሳታፊ የአብነት ተማሪ2፣ እድሜ18፣ የዜማ ተማሪ)፡፡

ተማሪዎቹ ቁራሽ ከምዕመናን ቤት ሲለምኑ ከውሻ ጋር መታገል፣ የበጋ ፀሐዩን፣ የክረምት ዝናቡን መታገስ ለረጅሙ የህይወትስኬት ፋይዳዉ የጎላ ነዉ፡፡ እንደዚህ አይነቱን ፈታኝ ሁነት

የሚጋፈጡት በልጅነታቸው በመሆኑ አለሙት ስኬት ላይ እንዲደርሱ የጥንካሬ መሰረት እንደሚሆናቸዉ ይገልጻሉ (ተሳታፊ የአብነት17፣ እድሜ22፣የቅኔ ተማሪ)፡፡ ከዚህ ዓይነቱ የትምህርት ህይወት በዓላማ መጽናትን፣ ለችግር አለመሸነፍን፣ ዕዉቀት ፈላጊነትን፣ መልካም ስነ ምግባርን እንደሚማሩበት መምህራኑ ይገልጻሉ፡፡ በአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ስርዓት ተማሪዎች እርስ በእርሳቸዉ መከባበር፤ እንግዳ ተማሪ ሲመጣ እግር አጥቦ፣ ቁራሽ አካፍሎ፣ መኝታ አጋርቶ አካባቢዉን ማላመድ ሞራላዊ ግዴታ ነዉ፡፡ ከአካባቢዉ ማኅበረሰብ አባላት ጋር ተከባብሮ መኖር የትምህርቱ አካል ነዉ፡፡ አንድ ተማሪ ከየትኛዉም አካባቢ ይምጣ ትምህርቱን ፈልጎ እስከመጣ ድረስ ዘሩ፣ ማንነቱ፣ ማኅበራዊ ደረጃዉም ሆነ አካባቢዉ መሰረት ተደርጎ የሚደርስበት ነቀፋም ሆነ ዉዳሴ የለም (ተሳታፊ መሪጌታ 16፣እድሜ 62፣የድጓ መምህር)፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ ትምህርቱ ዕዉቀትን ከማስጨበጥ በላይ ተማሪዎቹ በሰብዕናቸዉ እንዲታረቁ ፣ለማኅበረሰቡ አርዓያ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር ፋይዳዉ የጎላ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ስርዓት ማለፍ ተማሪዎች ለማኅበረሰባቸዉ በሚያበረክቱት ተሳትፎ ላይ በስራ መትጋትን፣ ጽናትን፣ ትዕግስትን፣ ለችግር እጅን አለመስጠትን፣ አስተዋይነትን፣ ሩቅ አሳቢነትን እና መሰል ጉዳዮችን የማላበስ አቅሙ ከፍ ያለ መሆኑን በዘርፉ የካበተ ልምድ ያላቸዉ መምህራን ይገልጻሉ (ተሳታፊ መሪጌታ 18፣ እድሜ 78፣ የቅኔ መምህር)፡፡ ሰራተኛ ንቦች ንግስት ንብን ከበዉ ለመስራት እንደሚፋጠኑት የአብነት ተማሪዎችም ከሊቁ (ከየኔታ) እግር ስር ቁጭ ብለው የማይነጥፈዉን የሊቃዉንቱን ዕዉቀት/ቀለም/ በመቅሰም ጣፋጭና ዘላለማዊ የሆነ ያሬዳዊ ዜማን /መንፈሳዊ ዕዉቀትን/፣ አገልጋይነትን፣ አርቆ አሳቢነትን ፣ሀገር ወዳድነትን፣ ታማኝነትን መማር መቻላቸዉ የዕዉቀትና የጥበብ ምንጭ የሆኑ አሻጋሪ ባለራዕዮችን ተከትሎ ሀገርን ማሳደግ እንደሚገባ ከትምህርቱ ፍልስፍና መረዳት ይቻላል፡፡

በአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ሂደት አንድ ተማሪ በእያንዳንዱ የትምህርት እርከን ስር የተቀመጡትን የትምህርት ጭብጦች ጥንቅቅ አድርጎ ማወቅ ይጠበቅበታል (ተሳታፉ21፣ እድሜ72፣ የድጓ መምህር)፡፡ በአስተማሪዎቹ በቡድን የሚሰጡትን ትምህርቶች በተናጠል ቀን እና ማታ ማጥናት ይኖርበታል፤የተሻለ አቅም ያላቸዉ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከአንድ የትምህርት እርከን ወደ ሌላኛዉ ሊዛወሩ ይችላሉ፡፡ ወሳኙ ጉዳይ ተማሪዉ በእያንዳንዱ የትምህርት እርከን ስር ያሉትን ይዘቶች ጥንቅቅ አድረጎ ማወቁ ላይ ነዉ፤ይህ ደግሞ በአንድ ጊዜ ትምህርት የጀመሩ ተማሪዎች እንድ አቅማቸዉና ችሎታቸዉ የትምህርት ማጠናቀቂያቀ ሰዓታቸዉ ይለያያል (በርግጥ መማር የሚፈልጉት የትምህርት እርከን መለያየቱ እንዳለ ሆኖ)፡፡

በአጠቃላይ የአስተምህሮ ስርዓቱ ተማሪዎች መማር በሚፈልጉት የትምህርት እርከን ደረጃ የመለያየት ሁኔታ ቢኖርም፤ በአንድ የእርከን ደረጃ ስር የሚማሩ ተማሪዎች በጊዜ ገደብ ሳይወሰኑ በችሎታቸዉ መሰረት እንዲጓዙ መደረጉ የተወዳደሪነትን መንፈስ ከማጎልበቱም በተጨማሪ በየደረጃዉ የተቀመጡ የትምህርቱን ይዘቶች በሚገባ አጣርቶ ለመሄድ እንደ በጎ ተሞክሮ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተለይ በአሁኑ ሰዓት አገራችን ለገጠማት የትምህርት ጥራት

መንገደል ያለዉ አበርክቶ የጎላ ሊሆን ስለሚችል ለፓሊሲ አጥኝዎች እንደግብዓት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 3.2. የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች

የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች እራሳቸዉን በቻሉ የትምህርት የእርከን ደረጃዎች ተከፋፍለዉ እንደሚሰጡ ይገለጻል (ተሳታፊ 12፣ እድሜ 78፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር)፡፡

### 3.2.1. የንባብ ቤት

በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ፊደል፣ ንባብ፣ ዳዊትና የመጀመሪያ ደረጃ የዜማ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ቀን ቀን ፊደል፣ አቡጊዳ፣ መልዕክተ ዮሐንስ እና ዳዊትን በቅደም ተከተል አስራ አምስቱን ነቢያትና መኃልየ ሰሎሞን ጨምሮ ትክክለኛውን የንባብ ስልትን በመከተል ማለትም በመጀመሪያ ፊደልን በማጋዝ፣ በመቀጠል በውርድ ንባብ ከዚያ በኋላ በቁም ንባብ በማንበብ በተገቢው መልኩ በጥንቃቄ ሰያፍ፣ ተነሽ፣ ተጣይ፣ የሚላላና የሚጠብቀውን ቀለም (ቃል) ለይተው በማወቅ ሲያጠኑ፤ ሌሊት ሌሊት ደግሞ በቃል በመሸምደድ (ደጋግሞ በማለት) ዜማን ይማራሉ፡፡

### 3.2.2. የቅዳሴ ቤት

ቅዳሴ ቤት ውስጥ ተማሪዎች በርካታ የቅዳሴ ዓዞችን የሚማሩ ሲሆን፤ ግብረ ዲቁንና እና ለቅስና የሚያበቃቸዉን ስርዓተ ጸሎት፤ ኪዳንንና ሰዓታትን (የሰዓታት ደራሲ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሲሆን መጽሐፈ ምስጢርን፣ አርጋኖን ድንግልና ሰዓታትን) በስርዓት ከነሙሉ ዜማቸው ይማራሉ፡፡

### 3.2.3. የዜማ ቤት

ይህ ትምህርት በቀጥታ ከቅዱስ ያሬድ ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጻዋትወ ዜማውን እንደደረሰው ስለሚያስነብቡ 6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማለት ደግሞ ከ500-599 ድረስ ስለሆነ በ505 ዓ.ም ተወለዱ ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሰናል፡፡ የሆነው ሆኖ ቅዱስ ያሬድ ከአጎታቸው ከአባ ጌድዮን ዘንድ ትምህርታቸውን የተማሩ ሲሆን፤ ከእሳቸው በተጨማሪ በወቅቱ ተሰዓቱ (9ኙ) ቅዱሳን ከተለያዩ ዓለማት ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ጊዜ ስለነበር ከእነሱ መካከል ከሆኑት ከአቡነ አረጋዊ ጭምር እንደተማሩ ይተረካል፡፡ በዜማ ቤት ከውዳሴ ማርያም ዜማ ጀምሮ መስተጋብዕ፣ አርባዕቱ፣ ሰለስት፣ ክስተት፣ አርአያም ሌሊት ሌሊት ሲሰጡ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍና ዚቅ ደግሞ በቀን ይማራሉ፡፡ የዜማ የአዛዚያም ዓይነቶችም በሶስት የተከፈሉ ሲሆን ግዕዝ፣ ዕዝልና አራራይ እንደሚባሉ ይገለጻል (ተሳታፊ 16፣እድሜ 78፣የዜማ መምህር)፡፡

### 3.2.4. የአቋቋም ቤት

በአቋቋም ቤት የአብነት ተማሪዎች ክብረ በዓል፣ ወርሃ በዓል፣ መዝሙር፣ ለእመ ኮነ፣ መረግድ፣ ንዑስ መረግድ፣ዝማሜ፣ ጽፋትና ወረብ ይማራሉ፡፡ የዜማ መንገዱም ቤተልሄም፣ ቆሜና አጫብር በመባል ይታወቃል፡፡ ለእነዚህ የዜማ ዓዞች ለጩኸት የሚያገለግሉ አስር ምልክቶችን የተዘጋጁ ሲሆን፤እነሱም፡-ይዘት ፣ ደረት፣ ቅናት፣ ጭረት፣ ድፋት፣ቁርጥ ፣ ሩጥ ፣ ርክርክ ፣ሂደት እና ሰረዝ መሆናቸዉ ይገለጻል (ተሳታፊ 2፣እድሜ 45፣የአቋቋም መምህር)፡፡

### 3.2.5. የቅኔ ቤት

መረጃ ሰጭ (ተሳታፊ 5፣እድሜ 58፣የቅኔ መምህር) የሆኑት ስለቅኔ ምንነት ሲገልጹ ቅኔ ማለት በአጭሩ ትርጓሜው ሰው ከራሱ አንቅቶ ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና ለማቅረብ ባሰበ ጊዜ ምሳሌ መስሎ ፤ምስጢር አመስጥሮ፤ ቃላዊ ግጥም በመግጠም፤ የልቡናውን ዕውቀት የአዕምሮውን ርቀት (ምጥቀት) የሚገልጽበት የሰማያዊ ልቡናን የሚያነቃቃበትና የሚያራቅቅበት ድርሰት ማለት ነው፡፡ ዋድላዎች ቅኔን የጀመረው ቅዱስ ያሬድ[2] ነው የሚለውን ታሪክ ሲያምኑ፤ ሌሎች ደግሞ ተዋናይ ወይም ደቀ እስጢፋ የተባለ የጎጃም ተወላጅ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ የእነዚህ የሁለቱ መረጃ በየበኩላቸው የዋድላ አገባብ፤ የጎጃም አገባብ፤ የዋድላ ቅኔ፤ የጎጃም ቅኔ እየተባለ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወርድ ሲወራረድ የቆየ ዛሬም ያለ ነገር መሆኑን ሊቃዉንተ ቤተክርስቲያን ይገልጻሉ (ተሳታፉ 9፣ እድሜ 75፣ የቅኔ መምህር)፡፡

በቅኔ ቤት ምስጢራዊ የሆኑ ጉዳዮች የሚመረመሩበት፣ የአስተሳሰብ ችሎታ በሰፊው የሚሻሻልበት፣ ከፍተኛ የሆነ የፍልስፍና እና የምርምር ትምህርት የሚሰጥበት፣ ነገሮችን በትኩረትና በተለያየ እይታ የማየት ልምድ የሚዳብርበት እና የፈጠራ ችሎታ በስፋትና በጥልቀት የሚለመድበት ቦታ ነው፡፡ በቅኔ ቤት ውስጥ መበጀመሪያ ግስ ይገሰሳል፤ በመቀጠልም ታሪክ ይተረካል፤ በመጨረሻም ቅኔ ይዘረፋል፡፡ አንድ የአብነት ተማሪ በዚህ የትምህርት ቆይታው ውስጥ ቅኔን ከነአገባቡ በስርዓት የሚማር ሲሆን፤ ከጉባኤ ቃና ጀምሮ እስከ እጣነ ሞገር ድረስ ማለትም በቅደም ተከተል ጉባኤ ቃና፣ ዘአምላኪየ፣ ሚበዝኑ፣ ዋዜማ፣ ሥላሴ፣ ዘይእዜ፣ መወድስ፣ ዐቢይ ኩልክሙ መወድስ፣ ክብር ይእቲ እና እጣነ ሞገር ከነሙሉ ዜማው የሚማር መሆኑ ይገለጻል (ተሳታፊ 15፣ እድሜ 68፣ የቅኔ መምህር)፡፡

### 3.2.6. የመጻሕፍት ትርጓሜ ቤት

በዚህ ትምህርት ቤት የቅዱሳን መጽሐፍት ትርጓሜ ማለትም፡- መጽሐፈ ብሉይ፣ መጽሐፈ ሐዲስ፣ መጽሐፈ መነኮሳት እና መጽሐፈ ሊቃውንት ዘሩን ከነትጓሜው (ከነ አንድምታው) ይሰጥበታል (ተሳታፊ 19፣እድሜ 76፣የመጽሐፍ ትርጓሜ መምህር)፡፡

### 3.2.7. የአቡሻክር ቤት

ይህ ትምህርት ቤት የስነ ክዋክብት[3] ፣ የዘመን አቆጣጠር፣ የረቀቀ ሒሳብ፣

---

*5.በዚህ ሀሳብ ተክለየስሱስ ዋቅጅራም ይስማማሉ፡፡ በተክለ ኢየሱስ አገላለጽ ቅዱስ ያሬድ የስንፍና እና የኢትዮጵያ ድኅነት ምንጭ ነው፡፡ ሥርግው የተክለ ኢየሱስን አገላለጽ እንደሚከተለዉ አስፍረውታል፤"በዚያውም ወራት ፩ ድምጸ መልካም ደብተራ ተነሳ፡፡ በግዕዝ ቋንቋ የሚዘፍን፡፡ … ስሙ ያሬድ ነው፡፡ … የያሬድ ዜማ ከተጀመረ ወዲህ በኢትዮጵያ ትምህርት ጠፋ፡፡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሕጻናቱም ኑሮዋቸውን ብቻ በዜማና በቅኔ አድርገውት ይኖራሉ፡፡ ሌላ ትምህርት አላገኙም፡፡ … ደግሞ የያሬድ ጥበብ ብዙ ሰው አቦዘነ፡፡ የቅኔውም ግጥም የተጀመረ በዚያ ወራት ነው፡፡ … የቅኔ ብልሃት ኢትዮጵያን አደኸየው፡፡ ፩ ሰው ቅኔ ሲማር ፲ ዘመን ተቀመጠ፡፡ በሰው አሳብ ቁራሽ እየለመነ ላይረባ እድሜውን በከንቱ ጨረሰው" ይላሉ (ሥርግው፣ 2002፡ 19-20)፡፡*

*6.ኮከብ ቆጠራ ከፍተኛ የሆነ የዕውቀት ዘርፍ እንደሆነና በከፍተኛ የትምህርት ተቋምና የጥናት መስኮች ውስጥ ጥናት ይደረግበታል፡፡ተመራማሪዎችም በዚህ ዘርፍ እስከ ከፍተኛ አካዳሚክ ማዕረግ ድረስ ይዘልቁበታል።አስትሮሎጂ "የጠንቋይ ስራ" አለመሆኑን የምንረዳው ‹‹ጥንቆላ›› አስማትና ምትሀት ከአስትሮሎጂ ጋር ተቀላቅለው (ለጥፋትና ለማጭበርበሪያ ዘዴ) ያዳበሩት በአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን የመካከለኛው ምስራቅ አገራት ነበሩ፡፡ ይህም*

*የአስትሮሎጂ ጥናት ላይ የራሱን መጥፎ ጥላ አጥልቷል። ‹‹በአሁኑ ጊዜ ማጂካል (ምትሀታዊ) አስትሮሎጂ ጊዜ ያለፈበትና ምንም ጥቅምና እውቀት የሌለበት እንደሆነ ታውቋል›› ሲሉ ዶክተር አብነት ስሜ በመጽሐፋቸው ገጽ 283 ላይ አስፍረዋል፡፡የዶ/ር አብነት ስሜ መጽሐፍ መግቢያ ዐረፍተ ነገር እንደሚለው አስትሮሎጂ ኮከቦች (12ቱ ነገደ ከዋክብት) በሰው ልጆች ስብዕና ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ የሚያጠና ሲሆን በርካታ ዘርፎችም (ለምሳሌ የህክምና አስትሮሎጂ) ቀደምት የጥናት መስክ መሆኑን ያመላክታል።ስለራሳችን፣ ስለምናውቃቸው እና ስለጓደኞቻችን ብዙ አስደሳች እና ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችለናል። ራሳችንን ለአዳጋ ሊከሰቱ ከሚችሉ ነገሮች ለመጠበቅ ያግዛል፡፡ ዶ/ር ሮዳስ ያበረከተው “አንድሮሜዳ” መጸጽሐፍም ይንንኑ ያረጋግጣል፡፡*

*ኮከብ (Astro — “logy” ሲጨመርበት “Astrology” በመሆን ወደ ጥናት መስክነት (ሥነ-ኮከብ ወይም የኮከቦች ሳይንሳዊ ጥናት) ከፍ የሚል ሲሆን፤ ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጠ የባህርይ፣ የተግባር፣ የማንነት መገለጫ የሚመስለን ቁጥራችን ቀላል አይደለም። እንደ ባለሙያዎቹ ድምዳሜ ከሆነ ይህ “ስህተት” ነው። ማንኛውም አካል ኮከብ አለው፤ በዛ ኮከቡና ኮከብ ቆጣሪው አማካኝነት ባህሪይው፣ አመሉ፣ ማንነቱ፣ ተክለ ሰውነቱ፣ ጤናው ይመዘናል፡፡ ይለካል፤ ይፈተሻል። ከዶ/ር አብነት ስሜ “ፍካሬ ኢትዮጵያ” መጽሐፍም የምንረዳው ይህንኑ ነው።በበርካታ ጥናቶች ላይ ስንመለከት እንደ ኖርነው፣ ኢትዮጵያ ለዓለም ያበረከተችው አለ ከማለት ያላበረከተችው የለም ማለቱ ይቀላል። ሌላው ቀርቶ ከዚህ ከሥነ-ኮከብ ጥናት አኳያ ያለውን ብቻ ብንመለከት የአስተዋፅኦዋ መነሻ አሻራ ከ“ዓውደ ነገሥት” መጽሐፍ ይጀምራል። እዛ ላይ ሁሉም ተብሏል፡፡ ሁሉም ተገልጿል። ምናልባት በአሁኑ ዘመን መነፅር ተመልክተን ይህ ይጎላል፤ ይህ ይበዛል ካላልን በስተቀር።*

*በዶ/ር አብነት መጽሐፍ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ ከሰጣቸው የመረጃ ምንጮቹ አንዱ ይሄው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሊቃውንት ውጤት የሆነው ዓውደ ነገሥት ነው። ይህንኑ ተንተርሰው የውጪው ዓለም ቀደምት ምሁራን አስፈላጊውን ጥናትና ምርምር ካደረጉ በኋላ ስለዚሁ መጽሐፍና ስለ ኢትዮጵያ ብሎም ኢትዮጵያዊያን አስተዋፅኦ በጉልህ ያሰፈሩት በዚሁ መጽሐፍ ላይ እንደ ወረደ፣ በመገኛ ቋንቋው በመጽሐፉ አባሪነት ተያይዞ ይገኛል። ዶክተር አብነት በመጽሐፋቸው ገጽ 386 ላይ በ“ድህረ ቃል” ስር “አልበርት ፓይክ ስለ ኢትዮጵያ የአስትሮሎጂ ጥበብ ጀማሪነት” በ1871 ያሰፈሩትን፤ በገጽ 389 ላይ “ጆን ጃክሰን ስለ ኢትዮጵያ የአስትሮሎጂ ጥበብ ጀማሪነት (“The Ethiopians were the first who invented the science of Stars” (1926) በሚል ርእስ) የጻፈው” እና ሌሎችንም በዋቢነት አስፍሮ እናገኛለን። በዚህ ውስጥ የተጠቀሱትም ሆነ ያልተጠቀሱ ሌሎች በርካታ ስራዎች መረዳት የሚቻለው ኢትዮጵያ በየዘርፉ የነበራትን ዕውቀት ብቻ ሳይሆን የነበራትን ተጽዕኖ*

የብርሃናት ምልልስ እና የመሳሰሉት ጠጣር (ውስብስብ) የትምህርት ዓይነቶች የሚሰጡበት ነዉ፡፡ ከዘመን አቆጣጠር ጋር ተያይዞ በዋናነት ተጠቃሽ የሆኑት ሊቅ አባ ዲሜጥሮስ ናቸዉ፡፡ አበቅቴውንና ህፀፁን በመለየት ሰባቱን አጿማት የሚያወጡበት የትምህርት ዘርፍ ነዉ፤ ከከዋክብት ባህሪ አንጻር በጣና ደሴት ላይ የተዘጋጀ እንደሆነ የሚነገር ሲሆን፤ ደራሲውም ዘረደሸት እንደሆነ ሊቃዉንቱ ይገልጻሉ (ተሳታፊ 3፣እድሜ 62፣የመጽሐፍት ትርጓሜ መምህር)፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል ለማሳየት እንደተሞከረዉ የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች ሰባት (7) እርከኖች ያሉትሲሁን፤ በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ማወቅ የሚጠበቅባቸዉን መሰረታዊ ዕውቀት ሙሉ በሙሉ አጣርተዉ ሲጨብጡ ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላኛዉ ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡ ተማሪዎች ክትምህርቱ ጎን ለጎን ገቢ በማግኘት ራሳቸዉን ለመደገፍ የተለያዩ ጥበባትን (ሙያ) ይቀስማሉ፡፡

## 3.3. የአብነት ትምህርት ጥበባዊ ፋይዳዎች

የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ስርዓት ከመንፈሳዊ ትምህርት ባሻገር በርካታ ጥበባት የሚከወኑበት ሲሆን ፤ክዋኔዎቹ ለማኅበረሰቡ ትልቅ እሴቶች ናቸው፡፡ ከአብነት ትምህርት ከሚመዘዙ ጥበባት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

*ፈጣሪነት፣ የነበራትን የፍልስፍና ደረጃ፣ የነበራትን ዓለም አቀፍ ብስለት፣ ከሁሉም በላይ የነበራትን የተፈጥሮ ዕውቀት ነው።*




ከአቡሻኽር መሻህፍት ላይ የተወሰደ

### 3.3.1. የብራና አዘገጃጀት

በብራና አዘገጃጀት ሂደት በመጀመሪያ ደረቁም ሆነ እርጥቡ የእንስሳ ቆዳ ይሰበሰባል፤ በዘመኑ የእንስሳት ቆዳ በዋናነት የፍየል፣ የፈረስ፣ የበግ፣ የጥጃ እና የሌሎችም ቆዳዎች ለብራና ጽህፈት እና ስዕሎች አገልገሎት የመጀመሪያ ተመራጮች ናቸው፡፡ እንደሚዘጋጀው የብራና ጽሑፍ ወይም የቁም ጽሑፍ አይነት መጠኑ ይለያያል፡፡ እንደ ስንክሳር፣ ገድላት፣ ድጓ አይነት የብራና መጽሐፎች ከከብት እና ከፈረስ ቆዳ በተዘጋጀ ብራና ይዘጋጃሉ፡፡ ሌሎች እንደመጠናቸው ከፍየል፣ ከበግ፣ ከጥጃ የዘጋጃሉ፡፡ ከቆዳ አይነቶችም ሁሉም ለብራና ጽህፈት አይሆኑም፡፡ በአግባቡ በአባቶች ይመረጣሉ፤ቆዳዎች ቀለም የሚቀበል የማይቀበል በማለት ይለዩታል፡፡ በአባቶች የሙያ አገላለጽ መስረብ ይባላል፤ቀለም የሚቀበል ማለት ነው፡፡ ቆዳዎችን የሚመርጡበት ምክንያት ጽሑፉ ከተጻፈ በኋላ እንዳይለቅ፣ እንዳይበላሽ፣ እንዳይቀደድ ቀድመው ለመንጠንቀቅና ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን በማሰብ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ (ተሳታፊ 11፣እድሜ 67፣የቅኔ መምህር)፡፡

ቆዳዎች በውሃ ይዘፈዘፋሉ፤ ቀጥሎም ከውሃ ወጥቶ በጠፍር መወጠሪያ ወይም ገመድ አራት ማዕዘን ባለው ጣውላ ላይ ይወጠራል፡፡ ከዚያም የቆዳው፣ ልፋጭ፣ ፀጉር በቀልማማ ቢላዋ ይገፈፋል፤ይላጫል፤ይራመማል፤ይደመጸጸል፡፡ለዚህ ተግባር የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ከብረት፣ ከድንጋይ ይዘጋጃሉ፡፡ ቀጥሎም የተደቀሰ ጨው እየተነሰነሰበትና ውሃም እንደ አስፈላጊነቱ እየተርከፈከፈበት በመራመሚያ ድንጋይ እየተራመመ ከልፋጩ ሁሉ ንጹህ ይሆናል፡፡ ቀጥሎም እንዲደርቅ ይደረግና በተዘጋጀው ምሳር ተፍቆ እንደገና ጨው ተደርጎበት ይራመምና ከዚያ በኋላ

ይደርቃል፡፡ ቀጥሎም የደረቀው ብራና በአስፈላጊው መጠን እየተለካ በመቀስ ይቆራረጣል፤ የጠቆረጠው በጥራዝ መልክ ይጠረዛል፡፡ ቀጥሎም ጥራዞቹ መስመር እንዲኖራቸው በማስመሪያ መሰል በሆነ ቀጭን ብረት ብራናዎችን አንድ በአንድ ይሰመራሉ፤ተሰምረው ካለቁ በኋላ ለጽሑፍ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡ የተጠረዘው በመዳመጫ እየለዘበ፣ እየለሰለሰ፣ የቁም ጽሑፍ ስራው እንደሚቀጥል ለማየት ተችሏል (ምልከታ፣ ጎዛምን ወረዳ፣ ቸር ተከል ቀበሌ፣ታህሳስ 24/2015 ዓ.ም)፡፡

### 3.3.2. የቀለም ቅመማ

የቀለም ቅመማ [4] የተለያዩ ቅጠሎችን በማድረቅና በማቃጠል፣ ከከሰል፣ ከምጣድ፣ ከሚራገፉ የተለያዩ ጥላሸቶችና ጥቀርሻዎች፣ ከስንዴ፣ ከበቆሎ፣ ከገብስና ከመሰል የአዝርዕት አይነቶች ይዘጋጃሉ (ምልከታ፣ ጎዛምን ወረዳ፣ ሊባኖስ ቀበሌ፣ጥር 5/2015 ዓ.ም)፡፡ የተለያዩ አዝርዕቶችን በማሳረር፣ በመቀቀል፣ በመዘፍዘፍ ከስድስት ወራት እስከ አንድ ዓመት ከፍተኛ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ያዘጋጃሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ተቀላቅለው ማሰሮ ውስጥ ከከተቱት በኋላ እስኪብላሉ (እስኪቦኩ) ድረስ በየጊዜው በጥቁር ገብስ እየታሹ ከስድስት ወራት አስከ ዓመት ሁለት ዓመት ድረስ ይቆያሉ:: ከእነዚህ የቀለም ቅመሞች ሌላ የደረቀ አበባና ስራ ስርም ከሙጫ ጋር ቀላቅለው ቀለም በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንደሚያዉሉ ይገለጻል፡፡ የተቀመሙት ነገሮች ተወቅጠውና ተደቁሰው እየታሹ የሚቆዩበትም መንገድ አለ፡፡ ቀለሙ እየቦካ ሲሄድም የማጣበቅ ጠባይ ይኖረዋል፡፡ ከዚያም በንፁህ ጨርቅ እንዲጠቀለል ይደረጋል፡፡ ብራናውን ማዘጋጀቱ በቂ ዕውቀት እንደሚጠይቀው ሁሉ ቀለም መቀመሙም ዕውቀትን፣ ችሎታንና ትዕግስትን የሚጠይቅ ሥራ መሆኑን አባቶች ያስረዳሉ (ተሳታፊ 9፣እድሜ 75፣የቅኔ መምህር)፡፡

---

*7. ለተጨማሪ ንባብና ማጠናከሪያ የሞገስ ሚካኤልን (2012) የሶስተኛ ዲግሪ ጥናት ይመልከቱ!፡፡*



*በረዳት መረጃ ሰብሳቢ፣ከተሳታፊ መሪጌታ9፣በቀን25/2015 ዓም ከሊባኖስ ቀበሌ የተነሳ ፎቶ ግራፍ*

መረጃ ሰጪዎች እንደሚገልጹት ጥንታዊያን ጸሐፊዎች ሽምበቆንና የመቃ ብርዕን እንዲሁም የትልልቅ አሞራዎችንና ንስሮች ላባ እንደ ብዕር አድርገው ለመጻፊያ ይጠቀሙባቸው ነበር። ሽምበቆውን ወይም መቃውን እንደሚፈለገው ዓይነት መካከሉን በመሰንጠቅ ይቀርጹታል፤ ከዚያም ባህላዊ ልምዳቸዉን በመጠቀም በተለያየ ደረጃ የተዘጋጁ ብራናዎችን፣ ቀለሞችን እና ብዕሮችን እያዋሀዱ ኢትዮጵያዊ የሆኑና ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉ፣ ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ በርካታ መጻሕፍትን በመጻፍ መንፈሳዊ አስተምህሮትን በዋናነት በጎንዮሽ ዓላማዊ ህይወትን ለመምራት የሚያስችሉ ዕውቀቶችን በብራናዎች ላይ በማቅለም ለትውልድ የሚያስተላልፉ መሆኑ ይነገራል (ተሳታፊ 13፣እድሜ 77፣የአቋቋም መምህር)።

### 3.3.3. መጻሕፍት መጠረዝ

መጻሕፍት መጠረዝ ሲባል በተናጠል ለጽህፈት የተዘጋጁ ብራናዎችን በሚፈለገው መጠን በማዘጋጀት መስፋት፣ ማያያዝ፣ ማገናዘብ፣ ተራ መስጠት፣ ገጽ መስጠት፣ ማለት እንደሆ ይገለጻል (ተሳታፊ 19፣ እድሜ 55፣የዜማ መምህር)። በመጀመሪያ የሚያይዙበት፣ የሚሰፉበት ራሱን የቻለ ባህላዊ የአሰራር ስርዓት አለው። መስፊያው ከእንስሳት ጅማት ይዘጋጃል፤ይህ ከሆነ በኋላ የብራና ጽሑፉ ወይም የቁም ጽሑፉን ከእንጨት ተጠርቦ፣ ተለሰለሶ በተዘጋጀ ገበታ እንዲጣበቅ፣ እንደያያዝ፣ እንዲጠረዝ ይደረጋል። ገበታው የሚዘጋጀው ከተመረጡ ሀገር በቀል ከሆኑ የዛፍ ዓይነቶች ከዋንዛ፣ ከወይራ፣ ከዝግባ፣ ከክትክታ፣ ከጨባ እና ከሌሎችም ጠንካራ የእንጨት ዓይነቶች ሲሆን፤ እንጨቶች ለረጅም ጊዜያት የደረቁ፣ ቅንቅን እንዳይበላቸው ወቅት ጠብቀው የተቆረጡና የተጠረቡ መሆን ይገባቸዋል።

ማጣበቂያዎች ከአዝርዕት ዓይነቶች ከአጃ፣ ከስንዴ፣ ከሙጫ፣ እና ከሌሎችም ግባቶች ጋር ተቀላቅለዉ ይገነፋሉ፤ በእሳት ይበስላሉ፤ ከዚያም ለማጣበቂያነት ይዉላሉ። የአጠራረዝ ስርዓቱ በጥንት አባቶች ሲሰራ የነበረ እና ጥንታዊ የብራና መጽሐፍት ይጠረዙበት የነበረ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ። በዚህ ሙያ ላይ የሃይማኖት አባቶች ድርሻ የጎላ መሆኑን መረዳት ይቻላል። የአሰራር ሂደቱን ዘመን ተሸጋሪ ለማድረግ ብራናውን፣ ቀለሙን፣ መጻፊያ ብዕሩን

ከማዘጋጀት ጀምሮ በጥንቃቄ፣ በልዩ ትኩረትና እውቀት የሚሰራ ጥበብ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡



በረዳት መረጃ ሰብሳቢ፣ከተሳታፊ መሪጌታ9፣በቀን25/2015 ዓም ከሊባኖስ ቀበሌ የተነሳ ፎቶ ግራፍ

### 3.3.4. መጻሕፍት መኮተት

መጽሐፍ መኮተት ሲባል ሀገር በቀል እውቀትን በመጠቀም የተጠረዘውን መጻሕፍት እንዳይበላሽ፣ እንዳይፈርስ፣ እንደይበታተን ከትውልድ ትውልድ እንደተላለፍ፣ ለብዙ ዓመታትና ዘመናት ዕድሜ እንዲኖረው በባለሙያ በጥሩ ሁኔታ በተዘጋጀ፣ በለፋ፣ በተፋቀ፣ በለሰለሰ፣ በተዳመጠ አረብ በገባ የከብት ቆዳ (በቀይ ቀለም የተነከረ ቆዳ) መለበድ፣ መሸፍን፣ መለበጥ፣ማሸግ መሆኑ ይገለጻል (ተሳታፊ 12፣ እድሜ 78፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር) ፡፡ አረብ የገባ ቆዳ ውበት እንዲኖረው፣ እንዳይደረቅ፣ እንዳይከር፣ እርጥበት እንዳይፈጠር የማድረግ ጥቅም አለው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉም አረብ በገቡ ቆዳዎች ይኮተታሉ ማለት አይደለም፡፡ ቀይ ቀለም ባልተቀቡ ቆዳዎችም የሚኮተቱ አሉ፡፡ የብራና ጽሑፍ ሲኮተት ወይም በከብት ቆዳው ማለትም በበሬና በላም ቆዳው ሲሸፈን ራሱን የቻለ የአስታሻሸግ፣ የአለባበድ፣ የአለባበጥ ሙያዊ ዕወቀት አለው፡፡ ቆደው በመጽሐፉ መጠን ልክ ተለክቶ እንዲቆረጥ ይደረጋል፡፡ ከተቆረጠ በኋላ በስንዴ፣ በገብስ ዱቄት በተገነፋ ግንፎ እንዲጣበቅ ይሆናል፤ ይህም ለተወሰነ ጊዜ እስኪለዝብ፣ እስኪያያዝ ፀሀይ እንዲየያገኘው ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም መያያዙ ሲረጋገጥ ከእንስሳት ጅማት የተዘጋጀዉ መስፊያ በቀጫጭኑ ተሸንሽኖ በወስፌ ወይም በመዋጥ የመጽሐፍቱን ጠርዞች ውብና ማራኪ በሆነ የአሰፋፍ ስልት እንዲያያዙ ይደረጋል፡፡

### 3.3.5. መጻሕፍ መደጎስ

በባህላዊ መንገድ የተጻፉ የብራና መጽሐፍት በመጠናቸው ትልቅ፣ መከካለኛና አነስተኛ ሆነው ከተኮተቱ በኋላ ይደጎሳሉ፡፡ መደጎሰ ሲባል የረጅም ጊዜ ልምድ፣ ዕውቀትና ችሎታ ባለቸው የመጽሐፍት ኮታቿች የተኮተተውን መጽሀፍ ቆዳው ሳይደረቅ ለዘብ እንዳለ የተለያዩ የቅርጽ ማውጫ መሳሪያዎችን

በመጠቀም በመጽሐፍቱ የፊት ለፊትና የጀርባ ሽፋን ላይ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ትምእዕርታዊ መልዕከት የሚያስተላለፉ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን በማውጣት መጽሐፍቱን ማጠንከር፣ ማስዋብ፣ ማስጌጥ፣ ትኩረት እንዲሰብ ማድረግ፣ ማሳመር መሆኑ ይታመናል (ተሳታፊ 5፣ እድሜ 68 ዓመት፣ የአቋቋም መምህር)፡፡ በመጽሐፍቱ ላይ እንዲወጡ የሚፈለጉ ቅርጻ ቅርጾች እንደመጽሐፍቱ መንፈሳዊ ይዘትና ጭብጥ፣ እንዲሁም እንደ ደጓሹ ልምድ፣ ችሎታና ዕውቀት የሚወሰን ነው፡፡

### 3.3.6. ባሕላዊ ህክምና

ባሕላዊ ህክምና ከእጽዋት፣ከእንስሳትና ከማዕድናት እየተቀመሙ ለጤና መጠበቂያ እና ለፈዉስ ህክምና የሚዉሉ መሆኑ ይገለጻል (ተሳታፊ 11፣እድሜ 67፣የቅኔ መምህር)፡፡ በባህላዊ ህክምና በሽተኞችን የመፈወስ ጥበብ የተገኘው ከአፋዊ ባህል (Oral Tradition) አሊያም ከመንፈሳዊ ስርዓት ጋር ተያይዞ ከሚከሰተው ጉዳይ (Majco-religious Manuscripts) እንደሚሆን ይገልጻል (Dawit and Ahadu፣1993፣2፤Dawit፣2003፣1)፡፡ በባህላዊ ሕክምና ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚሉት በኢትዮጵያ 80% የሚሆነው የሕብረተሰብ ክፍል ባህላዊ መድሃኒትን ለፈውስ ሕክምና ይጠቀማል Dawit and Ahadu፣1993)፡፡ ለባህላዊ መድሃኒት ግብአት የሚውሉ እፅዋት የሚሰበሰቡበት ወቅት በኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ባለሙያዎች ዘንድ በጳጉሜ ወር ረቡዕና አርብ የሚቆፈሩ መድሃኒቶች ፈዋሽነታቸው ከፍ ያለ ነው የሚል እምነት አለ (ተሳታፊ 13 ፣እድሜ 77 ፣የአቋቋም መምህር)፡፡ በአንጻሩ በእስልምና እምነት ተከታይ መድሃኒተኞች አመለካከት ለመድሃኒት ግብአት የሚያገለግሉ እፅዋት በየትኛውም ጊዜና ወቅት የሚሰበሰቡ መሆናቸው ይገለጻል፡፡ ይሁን እንጂ ጠዋት በባዶ ሆድ አቅል ሳይዛባ (አእምሮ ሳይዛነፍ) ለመድሃኒት የሚሆኑ እፅዋትን መቁረጡ የተመረጠ ሲሆን፤ የተለየ እምነትና አምልኮ ግን የሌለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለባህላዊ መድሃኒት የሚውሉ እፅዋት መቆረጥ አሊያም መቆፈር ያለባቸው በለጋ ዕድሜያቸው ወይም በስለው ካበቁ በኋላ ሳይሆን በመካከለኛው የዕድሜ ዘመናቸው ቢሆን ፈዋሽነታቸው አስተማማኝ እንደሚሆንም ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

ባህላዊ ባለመድሃኒተኞች ለፈውስ አገልግሎት የሚውሉ መድሃኒቶችን በተለያየ ቅርፅና መልክ አዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በሚታጠን፣በሚቀባ፣በሚታኘክ፣በሚሸተት ፣በሚጠጣ፣በሚቀበር፣በሚበላ፣በሚታሰር፣ በሚግሞጠሞጥ፣በሚታጠንእና በመሳሰሉ መንገዶች ይቀርባሉ፡፡ ከእፀዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት ውጤቶች ተቀምመው ለህሙማን የሚሰጡ መድሃኒቶች በአብዛኛው የሚወሰዱት ጠዋት በባዶ ሆድ እህል ውሃ ሳይቀመስ ነው፡፡ ባለመድሃኒተኞች የተለያዩ የመድሃኒት አይነቶችን ለህሙማን ቀምመው በሚሰጡበት ሰዓት መሻሪያውን ወይም ማርከሻውን አብረው እንደሚያዘጋጁ ለማወቅ ተችሏል፡፡ መሻሪያዎች ሁለት አይነት ናቸው፡፡ አንደኛው መድሃኒቶቹ እንዲሰምሩ የማያደርግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መድሃኒቶቹን ማርከሻ (ማፍረሻ) ነው፡፡ በአብዛኛው መሻሪያዎች የሚወስዱት ከምግብ በፊት ሲሆን፣ የእያንዳንዳቸውን ምንነት በምሳሌ አስደግፈን እንመልከት፡፡

ኮሶ ለተጣባው ሰው የእንቆቆ ፍሬ እንደተጠቃሚው ሰውነት ክብደትና ቅለት ከአንድ የሻይ ብርጭቆ እስከ ትልቁ የጠላ ብርጭቆ ድረስ እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ የተዘጋጀውን የእንቆቆ ፍሬ የሚጠጣው ሰው መራራነቱ እንዳያግደው ሲባል ሌሎች ታዳሚዎች እያጨበጨቡለት “ዶሮ ማታ፣ ዶሮ ማታ…” በሚለው ቃል ግጥም ያበረታቱታል፡፡ ይህም ግለሰቡ የተዘጋጀለትን የኮሶ መድሃኒት በሙሉ ልቡ (ያለ ፍርሃት) ጠጥቶ መድሃኒቱ በሽታውን ድል እንዲያደርግለት (እንዲያሽረው) ብርታትን ለመስጠት ታስቦ የሚረግ ነው፡፡ ከዚያም እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ እህል ውሃ እንዳይቀምስ ይከለከላል፡፡ መጨረሻ ላይ ወፍራም ጠላ (ዘመራ) ተጨምቆ ወይም ጠጅ ይሰጠዋል፡፡ ቀጥሎም ወፍራም ቡና ይጠጣል፡፡ ይህ እንግዲህ ለበሽተኛው የተሰጠው መድሃኒት በደንብ እንዲሰምር የሚያደርግ የመሻሪያ አሊያም የማርከሻ አይነት ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ክዋኔ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተግባራዊ እንደሚሆን አሉላ ፓንክረስት ገልጸዋል (2000፣96)፡፡ በሌላ በኩል አንድ ጨጓራውን የታመመ ሰው የግዜዋ፣ የጎርጠብ፣ የቡናና የፓፓየ ቅጠሎችን አንድ ላይ ደባልቆ እንደ ሻይ በማር አፍልቶ እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት ህመምተኛው ቶሎ ለመዳን በማሰብ አብዝቶ ቢጠጣ ህመምተኛው እንዳይጎዳ መድሃኒቱን ለማርከስ (እንዲከሽፍ ለማድረግ) አጓት እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ ይህ ደግሞ መድሃኒቱ በህመምተኛው ላይ ጉዳት ሳያደርስ እንዲረክስ የሚያደርግ ሌላው የመሻሪያ ወይም የማርከሻ አይነት ነው፡፡ ከተሰጡት ገለጻዎች ባህላዊ ባለመድሃኒተኞች፣መድኃኒቶች እንዳይረክሱ (ውጤታማ እንዲሆኑ) በባዶ ሆድ መወሰድ ያለባቸው መሆኑን በግልጽ ይታያል፡፡

ከመድሃኒት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ እጽዋት በሚሰበሰቡበት፣ በሚቀመሙበት ብሎም አገልግሎት ላይ በሚውሉበት ጊዜ ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ የሚያስፈልግ መሆኑን ይገልጻሉ (ተሳታፊ 5፣እድሜ68 ዓመት፣የድጓ መምህር)፡፡ እንዲያውም በቤተ ክህነት ትምህርት “እፅ የሃዩ ወእፅ ይቀትል” የሚል ብሂል እንዳለ ያስረዳሉ፡፡ ትርጉሙም “እፅ ያድናል፤ እፅ ይገድላል” እንደ ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የአብነት ተማሪዎች ጥበቡን እየተማሩ እነሱም በተራቸዉ እያስተማሩ ራሳቸዉንም ሆነ የማኅበረሰቡን ጤና ይጠብቃሉ፡፡ እግረ መንገዳቸዉንም ያለባቸዉን ኢኮኖሚ ችግር በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ ይጠቀሙበታል፡፡

በአጠቃላይ በአብነት የአስተምህሮ ስርዓት ተማሪዎች ከመንፈሳዊ ትምህርታቸዉ በተጨማሪ ዓለማዊ ህይወታቸዉን ለመምራት የሚያስችሏቸዉን ጥበባት ይቀስማሉ፡፡ የቀሰሟቸዉን ክሂሎች መሰረት በማድረግም በተማሪነት ህይወታቸዉ ለሚያጋጥሟቸዉ ፈርጀ ብዙ ችግሮች የመሻገሪያ ድልድይ ያደርጓቸዋል፤ እንደ ገንዘብ ማግኛ ስልትም ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ከጽንሰ ሀሳብ ዕውቀቶች በተጨማሪ የተግባር ልምምድም መተግበሪያ ዐዉድ ይሆናቸዋል፡፡ በህይወታቸዉ ለሚያጋጥሟቸዉ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ገጽታዎች በምን መልኩ መጋፈጥ ብሎም ማሸነፍ እንደሚቻል በተግባር ልምድ የሚያገኙበት ዘዴ በመሆን ያገለግላቸዋል፡፡ንድፈ ሀሳብን ከተግባር ጋር አዛምደዉ ለመማር ያስችላቸዋል፡፡

## 4. የአብነት ትምህርት አሁናዊ ተግዳሮቶች

የአብነት ትምህርት ቤት እጅግ ጥንታዊ፣ አገር በቀል፣ የራሱ የሆነ ስርዓት እና ወግ ያለው፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍና ሲወራረስ የኖረ ተቋም መሆኑ በዘርፉ ሊቃዉንት ይገለጻል (ተሳታፊ 5፣እድሜ 68 ዓመት፣የድጓ መምህር)፤ (መርሻ አለኸኝ፣2011)፡፡በአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ሂደት ውስጥ ከሚሰጠዩ ትምህርቶች ባሻገር በተቋሙ ልዩ የማኅበራዊ ህይወት ዕዉቀት የሚገበይበት፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ ህይወትን አጣምሮ ለመምራት የሚያስችል ጥበብ የሚቀሰምበት ስፍራ ነዉ፡፡

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት 25% የሚሆኑት የአብነት ተማሪዎች በወላጆችና በምዕመናን የሚደገፉ ሲሆን ፤ሌሎች 75% የሚሆኑት ደግሞ ምንም አይነት ድጋፍ የሌላቸዉ በመሆኑ ምግብ ፍለጋ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ለስራ እንደሚሰማሩ ይገለጻል(የማኅበረ ቅዱሳን ዳሰሳ ጥናት፣2014)፡፡ ይህ ሁኔታ ተማሪዎች ከትዉልድ አካባቢያቸዉ ርቀዉ፣ ከወላጆቻቸዉ ተነጥለዉ የመጡለትን ዓላማ ለማሳካት መሰናክል እንደፈጠረባቸዉ ይገልጻሉ (ተሳታፊ 17፣ እድሜ 18፣ የዜማ ተማሪ)፡፡ በተለይም የአብነት ትምህርት መስጫ ተቋማት ከነባሩ ልማድ ማለትም በገጠርና በጥንታዊ አድባራትና ገዳማት መሰጠታቸው ቀርቶ በከተሞች ዙሪያ እየተስፋፉ መሆናቸው ተማሪዎችንም ሆነ መምህራንን ለከተማ ህይወት የሚያጋልጡ ለአብነት ያህል በደብረ ማርቅስ ከተማ ዙሪያ በርካታ የአብነት ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ይህ ተግባር የአብነት ተማሪዎች ከመብዛታቸው የተነሳ በከተማው እየዞሩ ቁራሽ ለምነው የማግኘት እድላቸውንም የሚያሳንስ፣ ለመምህራን ደግሞ ትምህርቱን በገጠር ይሰጥ ከነበረው ባሕላዊ ዐውድ አውጥቶ ወደከተማ በማምጣት መስኩን እንደ ገንዘብ ማግኛ “business” እንዲቆጥሩ ያደረገው ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ትተው በከተማው በመዞር ቋጠሮ ሲሸከሙ፣ የቀን ስራ ሲሰሩ፣ ከሁሉም በላይ የከፋው ተግባር ደግሞ የውጭ አገር ኳስ ጨዋታዎችን ሲመለከቱ፣ ቁማር ሲጫወቱ፣ በስልኮቻቸው አልባሌና ባእድ ተግባራትን ሲመለከቱ ማየት ተለምዷል፡፡ የከተማው ማኅበረሰብ በኑሮው ጫና ምክንያት የተፈጠረበት ተግዳሮትና ከገጠሩ ለጋስነት አንጻር ሲታይ ደግሞ ንፉግነቱ እንዳለ ሆኖ፣በከተማው የአብነት ተማሪ ሳይሆን ከእነርሱ ጋር በመመሳሰል እየዞረ በመለመን የሚተዳደር ቡድን መኖሩም ትክክለኛ የአብነት ተማሪዎች በጥርጣሬ እንዲታዩና ቁራሽ እንዲነፍጋቸው ያደረገ ሆኗል፡፡ ከምንም በላይ ግን አብያተ ክርስቲያናትን ተገን አድርጎ የተንሰራፋው የካፒታሊዝም መንፈስ አደጋውን የከፋ አድርጎታል፤በተለይ በአጥቢያ ቤተክርስቲያኖች ዙሪያ የሚገኙ ቦታዎች የሰብል ማምረቻ እየሆኑ ከመምጣታቸዉ ጋር በተያያዘ ለመጸዳጃ የሚሆኑ ሽንት ቤቶች ባለመኖራቸዉ የአብነት ተማሪዎች በከፋ ስቃይ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል (የቡድን ዉይይት፣ ሊባኖስ ቀበሌ፣ ጥር 6/2015 ዓ.ም)፡፡ ተማሪዎቹ ያሉባቸዉን ችግሮች ተቋቁመዉ ትምህርታቸዉን ለመቀጠል በሚያደርጉት ብርቱ ትግል ዉስጥ ወደ ከተማ በመግባት የጥበቃ፣ የጉልበት እና የመሳሰሉትን ተግባራት በመከዎን በሚያገኙት ሽርፍራፊ

ገንዘብ እየተደለሉ ከትምህርት ገበታቸዉ የሚፈናቀሉ ቁጥራቸዉ ከእለት እለት እየጨመረ መምጣቱን የአብነት መምህራኑ በአጽንዖት ያብራራሉ (ተሳታፊ 3፣ ዕድሜ 62፣ የመጽሐፍት ትርጓሜ መምህር)፡፡ ቁጥራቸዉ ጥቂት የሚባሉ ተማሪዎች ያለዉን ጫና በመቋቋም ለዓለማቸዉ መሳካት እየተፍጨረጨሩ የሚገኙ ቢሆንም፤ ካላዉ አገራዊ ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር የተጋረጠባቸዉ ሳንክ ተቋማዊ በሆነ መልኩ መፍታት ካልተቻለ ጥንታዊ የአስተምህሮ ስርዓቱ በውስጡ ያሉትን ጥበቦች ይዞ ላይመለስ መክሰሙ የማይቀር ሀቅ መሆኑን ከመረጃ ሰጭዎች ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 5. ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና የይሁንታ ሀሳቦች ከጥናቱ ዉጤት በመነሳት ተደራጅተዉ የቀረቡበት ነዉ፡፡

### 5.1. ማጠቃለያ

በምርምሩ መነሻ ሃሳብ ላይ ለመግለጽ እንደተመከረው ጥናቱ **"የአብነት ትምህርት የአስተምህሮ ደረጃዎች፤ ጥበባዊ ፋይዳዎች እና አሁናዊ ተግዳሮቶች በጎዛምን ወረዳ ማኅበረሰብ ተተኳሪነት"** በሚል ርዕስ ትኩረት አድረጎ የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎችን ግብ ለማድረስ፣ የምርምር ጥያቆችን ለመመለስ አነሳሽ ምንያቶችን መነሻ በማድረግ በመረጃ ትንተናው ላይ የተገኙ የጥናቱን ውጤቶች ለመግለጽ ሞክሯል፡፡ የአብነት ትምህርት ወደ አዲስና ታላቅ ምዕራፍ የተሸጋገረዉ በ6ተኛው መቶ ክ/ዘ በተነሣዉና የመጻሕፍትና የዜማ ደራሲ በሆነው በታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ አማካኝነት መሆኑን ለመለየት ተችሏል፡፡ በአብነት ትምህርት ቤቶች ከሚሰጡት ትምህርቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፡- የንባብት ምህርት ቤት ፣የቋንቋ ትምህርት ቤት፣የዜማ ቤት፣የቅኔ ቤት እና የቁጥር ትምህርት ቤቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በአብነት ትምህርት ቤቶች የቁም ጽሑፍ፣ መጽሕፍ መጠረዝ፣ መኮተትና መደጎስ በመደበኛነት ባይሰጡም ከትምህርቱ ጎን ለጎን የሚገኙ ጥበቦች መሆናቸቨውን ለመገንዘብ ተችሏል፤ መጽሐፍ መኮተት፣ መደጎስ፣ባሕላዊ ህክምና እንዲሁም ሌሎች ዕውቀቶች ከአበው በትውፊት በመተላለፍ ዛሬ ላይ የደረሱ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት የመለውጥ ሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በተወሰኑ የአብነት ትምህርት ቤቶች በግል አባቶች፣ ዲያቆናት፣ መናኩሳት ጥበባቱ በመከዎን ላይ ይገኛሉ፡፡ በቅኔ ቤት የፈጠራ (Creativity) ወቅታዊ ሁኔታዎችን የመረዳት ችሎታ (Current perspective and understanding) ጎልቶ የሚታይበት መሆኑ፤ ታሪክን እና ወቅታዊ ሁኔታዎችን አገናዝቦ የማቅረብ ችሎታ እንዲሁም የፍልስፍና የአስተሳሰብ ትምህርት (Critical thinking) ያለበት፤ ቅኔ በመቶዎች የሚቆጠሩ መንገዶች ያሉት በመሆኑ እንደየ መንገዱ ልዩ ልዩ የአቀራረብ ስልትን ፣ የቋንቋን አገባባዊ መዋቅርን እና ቋንቋዊ ሙያን ለመማር እንደሚያስችል ተለይቷል፡፡ በአብነት ትምህርት ቤቶች የቁም ጽሁፍ፣ መጽሀፍ መኮተትና መጽኃፍ መደጎስ ላይ ዓለም አቀፋዊ ዘመናዊነት ተጽዕኖ ሀገር በቀል እውቀቱ ላይ በከፍተኛ ጫና እያሰደረባቸው ስለሆነ የመለወጥ እና የቀጣይነት ሂደታቸውን እንዲፋጥን እያደረገው መሆኑን የተለየ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት የአብነት ተማሪዎች ከምግብ አቅርቦት፣ ከመጠለያ እጥረት፣ ከአልባሳት እና ከመጸዳጃ ዉስንነት አንጻር

ችግሩን ተቋቁሞ ለመቀጠል በሚያደርጉት ጉዞ ላልተፈለገ አዳጋ እየተዳረጉ፤ትምህርቱንም እያቋረጡ መሆኑን ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል።

## 5.2. የይሁንታ ሀሳቦች

የአብነት ትምህርት ቤቶች አሁን ላለዉ የዘመናዊ ትምህርት መሰረት ናቸው። በተጨማሪም ያለፈውና ያሁኑን ትውልድ በመንፈሳዊ አስተምህሮት አማካኝነት በስነ ምግባሩ፣ በባህሉ፣ በወጉ፣ በትውፊቱ እንዲኮራ በማድረግ ሂደት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ይሁን እንጅ የአብነት ትምህረት ቤቶች በአሁኑ ጊዜ ያሉበት ደረጃ አሳሳቢ በመሁኑ ለቀጣዩ ትውልድ የአስተምህሮ ስርዓቱን እና ጥበባዊ እሴቶችን ማሻገር ይቻል ዘንድ ከጥናቱ የመነጩ የይሁንታ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ✓ የአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናት ለማድረግ የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ብዙ ጥናቶች በጥልቀት ተካሂደዋል ለማለት ያስቸግራል፤በመሆኑም የባህል ቱሪዝም ባለሙያዎች በትኩረት አጥንተዉ ከባለ ደርሻ አካላት ጋር በመነጋገር የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ቢፈልጉ፤
- ✓ የቤተክርስቲያኗ የሃይማኖት አባቶችና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሁኑ ተቋማት በዘርፉ ላያ የሚታዩ ተግዳሮቶችን በጥናት ላይ ተመርኩዞ ለመፍታት ተከታታይ እና ተለጣጣቂ የውይይት መደረክኮችን እንዲዘረጋ ቢደረግ፤
- ✓ የአብነት ትምህርት ተቋማት ባህላዊ ቅርስን እና ጥበባዊ እሴቶችን ለቱሪዝም መስህብ ከማዋል አንጻር ፋይዳቸዉ የጎላ በመሆኑ ቀጣይነታቸዉን ለማረጋገጥ ከባለድርሻ አካለት ጋር ተከታታይ ስራዎች እንዲከናዎኑ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ቢያደረጉ የተሸለ ይሆናል።

## 6. ዋቢ ጽሑፎች


ሀብተ ማርያም ወርቅነህ።(1963)። ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት። አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት።

ልዑለቃል አካሉ ዓለሙ። (2002)። ጥንታዊው የኢትዮጵያ የአብነት ትምህርት ቤት ከዘመናዊው ትምህርት ጋር ሲነጻጸር፤ አትላንታ ጆርጅያ ያልታተመ።

መርሻ አለኸ። (2011)። በእንተ ስማ ለማርያም፤ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት ይዘቱ፣ሥርዐቱ እና ሕይወቱ፤አዲስ አበባ።

መንግስቱ ለማ። (1959)። መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ።አዲስ አበባ።

መንግሥቱ ጎበዜ። (2002) በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ የኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት እና መዛግብት።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥናት መጽሔት፣ ቁ. 1 የቅዲ ፣መብት ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን።

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል። (1955)። አማርኛ ቅኔ።አዲስ በአበባ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ሰለሞን ተሸሞ። (2007)። ፎክሎር ምንነቱ፣የትኩረት አቅጣጫ። ፋር ኢስት ትሬዲግ ኃ.የተ. የግ. ማህ።

በኃሰው የሽዋስ። (2010 ዓ.ም)። የአፍ መፍቻ ቋንቋን በትምህርት መስጫነት የመጠቀም አመለካከቶችና ተግዳሮቶች፤ በስልጤ፣ በሀድያ፣ በከምባታና በወላይታ ቋንቋዎች ተተኳሪነት።

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ተሾመ የኋላሸት። (2009)። አጠቃላይ የጽሕፈት ሥርዓትና የፊደል ዳሰሳ ትኩረት በኢትዮጵያ የፊደል። Zena-Lissan Volume XXVI Number 1.

ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም። (1999)። ኦቶባዮግራፊ የሕይወት ታሪክ። አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ።

ኀይለ ኢየሱስ አለባቸው። (2010)። መጽሐፈ ሄኖክ በግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ያለው ቦታ በማብራሪያ የታገዘ ትርጉምና ትንተና።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥናት መጽሄት፣ቁ.፯ (ነንሴ ፳፻፲)፣ ጥናትና ምርምር ተ▯ ም፣ማኅበረ ቅደሳን።

ኀይለ ገብርኤል ዳኘ። (2007)። ባህልና ትምህርት በኢትዮጵያ። Studies on Education in Ethiopian Tradition. አዲስ አበባ፤አዲስ አበባ ዩኒቸርሲቲ ፕረስ።

አለቃ ተክለ እየሱስ ዋቅጅራ። (2003)። የጎጃም ትዉልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ(ግርማ ጌታቸዉ እንዳዘጋጀዉ)፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣አዲስ አበባ።

አለቃ ተክለ እየሱስ ዋቅጅራ። (2002)። የኢትዮጵያ ታሪክ (ዝግጅት፣ሐተታና አርትዖት ሥርግዉ ገላዉ)፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣አዲስ አበባ።

ጌታሁን ድምፀ። (2010)። ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ።አዲስ አበባ፤ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ፍሬህይወት ባዩ። (2002)። የኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገጽታ፤Zena-Lissan Volume XXVI Number.

ዘላለም ቻላቸው። (2011)። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክና እምነት አጭር ዳሰሳ።

ያለው እንዳወቀ። (1998 ዓ.ም)። የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። አዲስ አበባ፡ አልፋ አሳታሚዎች።

Catherine Dawso.(2002). Practical Research Methods, A user-friendly guide to mastering research techniques and project: First published in 2002 by How to Books Ltd, 3 Newtec Place, Magdalen Road, Oxford: United Kingdom

Dawit Abebe and Ahadu Ayehu.(1993). Medical Plants and Enigmatic Health Practice of Northern Ethiopia. Addis Ababa: Berhanenna Selam Printing Press.

Gabriella F. Scelta. (2001). The Comparative Origin and Usage of the Ge'ez Writing system of Ethiopia) https://eyobtilahun.wordpress.com/.

Muhiddin Muhammed. (June 2010). An Assessment of Traditional Islamic Education practices and Their Implications to Modern Education. A thesis submitted to the School of Graduate Studies of Addis Ababa University.

Mezmur Tsegaye. (211). Traditional Education of the Ethiopian OrthodoxChurch and Its Potential for Tourism Development (1975-present). In Patiial FulfIllment of the Requirements for the Degree of Master of Art in Tourism and Development. A Research Presented to the School of Graduate Study Addis Ababa University.

Oring Elliott. “Three Functions of Folklore: Traditional Functionalism as Explanation in Folkloristics.” University of Illinois Press, The Journal of American Folklore, Vol. 89, No. 351, pp. 65-80.

Pankhurst, Richard. (1969). Ethiopia chrch, state & education in Africa. Ed. Scanlon David G. Newyork: Teachers collage.